# በአማራ ክልል ከ183 በላይ ሰዎች መገደላቸውን የተባበሩት መንግሥት ድርጅት ገለጸ

By **አዲስ ማለዳ** - 31/08/2023



ሐሙስ ነሐሴ 25 ቀን 2015 (አዲስ ማለዳ) የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በአማራ ክልል በመንግሥት የጸጥታ ኃይሎች እና በፋኖ ታጣቂዎች መካከል እየተደረገ ባሉ ግጭቶች ከሐምሌ ወር ጀምሮ ቢያንስ 183 ያህል ሰዎች መገደላቸውን ገልጿል፡፡

የተባበሩት መንግሥታት ሰብዓዊ መብት ጽሕፈት ቤት ማክሰኞ ነሐሴ 22/2015 ባወጣው ሪፖርት፤ በአማራ ክልል በመከላከያ ሠራዊትና በፋኖ ታጣቂዎች መካከል የተፈጠረውን ግጭት ተከትሎ የታወጀው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አተገባበር እና በክልሉ ያለው የጸጥታ ሁኔታ ተባብሶ መቀጠሉ እንዳሳሰበው ጠቅሷል፡፡

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ለባለስልጣናቱ ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ ግለሰቦችን በቁጥጥር ሥር ለማዋል፣ የሰዓት እላፊ ገደብ ለመጣል እና ስብሰባዎችን ለመከልከል ሰፊ ስልጣን ሰጥቷቸዋል ነው ያለው፡፡

በአስቸኳይ አዋጁ መሰረት በኢትዮጵያ ከ100 በላይ ሰዎች መታሰራቸውንና ከታሰሩት መካከል “የፋኖ ደጋፊዎች ናቸው” ተብለው የሚገመቱት የአማራ ብሄር ተወላጆች በርካታ መሆናቸውንም ጽህፈት ቤቱ ገልጿል።

እንዲሁም በአማራ ክልል ያለውን ሁኔታ የሚዘግቡ ቢያንስ ሦስት ጋዜጠኞች ከተያዘው ነሐሴ ወር መጀመሪያ ጀምሮ ለእስር መዳረጋቸውንና መሰረታዊ መገልገያዎች በሌላቸው እስር ቤቶች ዉስጥ እንደሚገኙ ነው የጠቀመው።

መንግሥት እየፈጸመ ያለውን የጅምላ እስር እንዲያቆም፣ የነጻነት ገደቦችን እንዲያነሳና ያለምክንያት የታሰሩት ኹሉ እንዲፈቱ የጠየቀው ተመድ፤ “መንግሥት ዓለም አቀፍ ሕጎችና ደንቦች መከበራቸውን ማረጋገጥ አለበት።” ሲል አሳስቧል።

እንዲሁም ለኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽንና የተባበሩ መንግሥታት የሰብዓዊ መብት ጽህፈት ቤት የእስረኞች ማቆያ ቦታዎች ያለምንም ገደብ ክፍት እንዲደረጉ ጠይቋል።

የእስረኞች ደህንነት፣ ፍትሃዊ የፍርድ ሂደት እንዲሁም የዋስትና መብቶቻቸው በሙሉ ሊጠበቁላቸው እንደሚገባም ገልጿል።

ተመድ አክሎም የሚመለከታቸው አካላት ሞት፣ ሌሎች የመብት ጥሰቶችንና እንግልቶችን እንዲያቆሙ ያሳሰበ ሲሆን፤ አለመግባባቶችን በውይይትና በፖለቲካዊ ሂደቶች ሊፈቱ እንደሚገባ አመላክቷል።

በሌላ በኩል በምዕራብ ትግራይ የይገባኛል ጥያቄ ባለባቸው ቦታዎች አካባቢ ከ250 በላይ የትግራይ ተወላጆች በአካባቢው ባለስልጣናት እና ታጣቂዎች ጥምር ዘመቻ መታሰራቸውንም ገልጿል።

እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል ያለው የመብት ረገጣ እና በተደጋጋሚ የሚፈጸሙ ወንጀሎች ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ መሆኑን የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በሪፖርቱ ጠቁሟል።

በኢትዮጵያ የተለያዩ ክልሎች የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብት ረገጣዎችና ጥሰቶች ላይ አስቸኳይ ምርመራ ተደርጎ በኃላፊነት ላይ ያሉ አካላትን ተጠያቂ ማድረግ እንደሚገባም አሳስቧል።

---

---

**አዲስ ማለዳ**

*http://addismaleda.com*